# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በኢኦተቤክ

# መጽሐፍ ቅዱስ

1. ቅዱስ (ልዩ) መጽሐፍ ነው፡፡
   ሀ. የጻፉት ቅዱሳን ሰዎች ናቸው፡፡
   ለ. ያጻፋቸው እግዚአብሔር ነው፡፡ 2ኛ ጴጥ. 1:21
2. በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡
   ሀ. የብሉይ ኪዳን እና
   ለ. የሐዲስ ኪዳን
3. ብሉይ ማለት አሮጌ ወይም የጥንት ማለት ሲሆን ሐዲስ ማለት ደግሞ አዲስ ማለት ነው፡፡

# የብሉይ ኪዳን መሠረት መጻሕፍት

- ኦሪት ዘፍጥረት
- ኦሪት ዘጸአት
- ኦሪት ዘሌዋውያን
- ኦሪት ዘኍልቁ  እና
- ኦሪት ዘዳግም ናቸው::

አነዚህ መጻሕፍት በግዕዝ አምስቱ ብሔረ ኦሪት ይባላሉ ወይም በእንግሊዝኛ ፔንታቲዩክ ይባላሉ:: በዕብራይስጥ ደግሞ ቶራ ተብለው ይጠራሉ::ሌሎቹ መጻሕፍት ያንኑ ያጸናሉ እንጂ አዲስ ሕግ አይሰሩም::

# የሐዲስ ኪዳን መሠረት

- የማቴዎስ ወንጌል:- ማቴ.26:26
- የማርቆስ ወንጌል:- ማር.14:24
- የሉቃስ ወንጌል:- ሉቃ.22:20
- የዮሐንስ ወንጌል:-ዮሐ.5:53
- የሐዋርያት ሥራ: ሥራ: 2:38

# ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?

- ኪዳን ማለት «ውል» ማለት ነው::
- በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ቃል ኪዳን የሰጠበት ቦታ ብዙ ነው:-«ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ» እንዲል መዝ. 88፤3:: በዚህ ግን የምንመለከተው የኃጢአት ስርየት የሚገኝበትን ብቻ ነው:: ይህም ከደም መፍሰስ ጋር የተያያዘ ነው:-«ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም» እንዲል ዕብ. 9፤22::

# ብሉይ ኪዳን

- ኪዳን የሚመሠረተው በደም ነው::
  - ለአብርሃም የተሰጠውን የግዝረት ኪዳን ተመልከት:: ዘፍ. 17:1-14
  - በሙሴ በኩል ለእስራኤል የተሰጠውን ኪዳን ተመልከት:: ዘጸ. 24:1-8
- ነገር ግን የኃጢያት ስርየት ለማስገኘት ሙሉ አቅም አልነበረውም:: ዕብ. 10 1-18
- ሐዲስ ኪዳን እንደሚተካ ትንቢት ተናግሩዋል:- መዝ. 39:6-8፤ትን. ኤር.31:31-34

# የሐዲስ ኪዳን አገልግሎት

- የሚፈጸመው ዘወትር በሚካሔደው የቅዳሴ ስርዓት ነው::ሥራ: 2:42 ና 20:7
- በዚህም ቤተክርስቲያን ልጆቿዋን ለመንግስተ ሰማያት እንዲበቁ ታደርጋለች::
- ሌሎች የቤተክርስቲያን ስርዓቶችም የሚደመደሙት በቅዳሴ ነው::

# የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አከፋፈል

- አምስቱ ብሔረ ኦሪት
- ነቢያት
- የጥበብ መጻሕፍት
  - የቅኔ መጻሕፍት
  - የታሪክ መጻሕፍት
  - የትንቢትና የታሪክ በአንድ ላይ የያዙ

# የብሉይ ኪዳን ታሪክ

- የአዳም ተፈጥሮ፤ የአዳም መውደቅና ከገነት መባረር፤የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ በ አብርሃም:ይስሐቅ:ያዕቆብ: ወደ ግብፅ መሰደድ፤የሙሴ መነሳት፤በኢያሱ አማካይነት ወደ ከነአን መመለስ ታሪክ ነው።

## …

- ስለዚህም በብሉይ ኪዳን የሰው ልጅ ታሪክና የሃይማኖት ታሪክ ልዩነት የለውም፡፡ በተለይም የእስራኤል ታሪክ የእግዚአብሔር የማዳን ክንድ የተገለጠበት፤የመዳናችን ቅድመ ዝግጅት የተደረገበት፤ከሙሴ ኢያሱ ተረክቦ እስራኤልን ከነአን እንዳስገባ ክርስቲያኖችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግስተ ሰማያት እንደሚያስገባ የሚያመለክት የሰው ዘር ሁሉ ታሪክ ነው፡፡

# የእስራኤል መመረጥ

- በስልጣኔ በአካባቢያቸው ካሉ አሕዛብ (ለምሳሌ ባቢሎን:ግብፅ...) አይበልጡም ነበር ነገር ግን ሳባቶቻቸው በገባው ቃል መሠረት ከአሕዛብ ሁሉ መርጦ ከፍ አደረጋቸው:: ዘዳ. 7:8 ና 9:4
- ምርጫውንም በሲና ተራራ ላይ በእንስሳት ደም በቃል ኪዳን አተመው::
- ይህም በሁዋላ ዘመን ከአብርሃም ዘር በመንፈስ ለሚወለዱ ልጆች በመስቀል ላይ በልጁ በሐዲስ ኪዳን ደም እንደሚያትመው የሚያሳይ ነው::

# ይቆየን…

በሚቀጥለው ኦሪት ዘፍጥረትን እንማራለን፡፡